# በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

**ÄTHIOPISCH-ORTHODOXE KIRCHE IN DEUTSCHLAND**

Ückeratherstr. 2, D-50739 Köln
Tel./Fax.: 0221/ 599 2623
E-Mail: aeokd@gmx.de
www.aethiopisch-orthodoxe-kirche-deutschland.de

Bankverbindung:
Commerzbank
Köln
Kto.Nr. 1121383
BLZ: 370 400 44
Datum:21.7.12


ለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፤
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ም/ቤት ፕሬዝዳንት፣

ሐምሌ ፲፬ ቀን 2004 ዓ.ም.

በቅድሚያ መንፈሳዊ ቡራኬዎ እንዲደርስኝ እለምናለሁ።
ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን፣

**ጉዳዩ እ.ኢ.አ. ሐምሌ 2 ቀን 2004 ዓ.ም. በኢሜል የተላለፈልኝን ደብዳቤ ይመለከታል**

ደብዳቤው ከቅዱስነተዎ ለእኔ ምስኪን ለመሆን የመንፈስ ቅዱስ ልጅዎ የተላከ በመሆኑ መልስ ለመስጠት በምዘጋጅበት ጊዜ የቃላት አጠቃቀሜን ሊገድብብኝ እንደቻለ ለቅዱስነትዎ በቅድሚያ ሳልገልጽ አላልፈውም። በ20 ዓመታት ውስጥ ባልተለመደ መልኩ በፍራንክፈርት ከተማ ለማድረግ የታሰበውን ሰላማዊ ሰልፍ በተመለከተ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ቆንስላ ጽ/ቤት የቀረበለዎትን ሪፖርት መሠረት በማድረግ በቁጥር ል/ጽ/556/143/04 በ2/11.2004 ዓ.ም. የተጻፈው ደብዳቤ ደርሶኛል። ከዚሁ ላይ መጠቆም ያለብኝም፣ ከቆንስላው ጋር በጉዳዩ ላይ ለመነጋገርና ውይይት ለማድረግ ቀጠሮ ይዘን ባለንበት ሁኔታ ተገናኝተን ሳንነጋገር በዋዜማው በጎን ቆንስላው ከቅዱስነትዎ ይህን የመሰለ ዕዳ ደብዳቤ በማጻፉ በኢምባሲያችን ላይ እምነት እንዳይኖረን የሚያደርግ ነው። እጅግ የምደክምላት ቤተ ክርስቲያኔንና እኔን ከሚወክል አካል ይህን የመሰለውን ደብዳቤ በማጻፉ ጥልቅ ኃዘን ተሰምቶኛል። ፈረንጆች " እራስን ማመስገን ይገማል" እንደሚሉት ካልሆነብኝ በስተቀር በልዑል እግዚአብሔር ፈቅድ ብሔራዊ ግዳጄን ሲፈጽም በኖረና በሚኖር፣ በጀርመን ላለችው ቤተ ክርስቲያን መልካም ገጽታን ባተረፈ፣ በአውሮፓ ለተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናት ፋናወጊ በሆነ፣ ከእናት ቤተ ክርስቲያን እንዳይለዩ ያላቋረጠ ጥረት ባደረገ፣ በብዙ መሥዋዕትነት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን እንዲገዛ አድርጎ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ባስረከበ ካህን ላይ የተደረገው ሁሉ ከሰብኣዊ አንጻር ሲታይ የማይታመን ነው። መከራዬን ብቻ ሳይሆን ጸጋዬንም ስለምቆጥር በደስታ እቀበለዋለሁ።

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን

የተጻፈልኝን ደብዳቤ በተመለከተ፣ የተለመደው አባታዊ ርኅራኄዎ ሳይለየኝ ለግንዛቤ ይረዳል ብየ ያሰብኩትን እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

፩ኛ/ ሪፖርቱን ያቀረበለዎ አካል እንደሚለው ሰዎችን የሰላማዊ ሰልፍ ተባባሪ እንዲሆኑ ያለፍላጎታቸው በማስገደድ ላይ የምገኝ መሆኔን እንዲረዱት ያደረገዎ መሆኑን ገልጸው፣ ይህ ዓይነቱ አሠራርም ኢ-ቀኖናዊና ኢ- ዲሞክራሲያዊ ብቻ ሳይሆን ካህናቱን ለሁከትና ለብጥብጥ የሚዳርግ እንቅስቃሴ እያደረግሁም እንደ ሆነ ያሰሙሩበትን ከጥልቅ ኃዘን ጋር ልብ ብየዋለሁ። ከዚህ ሌላ ሪፖርቱን ያቀረበለዎ መንግሥታዊ አካል በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የሃይማኖት ነፃነት የተሰጠ መሆኑን እያወቀ በእኔ በካህኑ ላይ እንደዚህ ያለ ጣልቃ ገብነት በማድረግ ከሳሽ ሆኖ መቅረቡ ሌላው አሳዛኝ ተግባርና ሕገ መንግሥቱንም የጣሰ ድርጊት ነው።

፪ኛ/ አሁንም ሪፖት ያቀረበለዎ የመንግሥት አካል የምንኖርበትን አገር ዲሞክራሲያው ሥርዓት ያውቀዋል ብዬ ስለማምን እንኳንስ የእኔ ብጤው ተራና ምስኪን ግለሰብ ቀርቶ መንግሥት እንኳን አንድን ግለሰብ ለምንም ጉዳይ ሆነ፣ በምንም ምክንያት ከሕግ ውጭ አስገድዶ አንድን ነገር እንዲፈጽም ሲያደርግ ቢገኝ ለፍርድ የሚቀርብበት ሀገር ስለሆነ፣ የሌለኝን፣ ሊኖረኝም የማልመኘውን የጉልበተኛ ባህርይ ቀለም ቀብቶ ለማቅረብ የተደረገው ሙከራ እኔንና ቤተ ሰቤን ያሳዘነ፣ ማኅበረ ካህናቱንና ማኅበረ መእመናኑን ያስደነቀና ያስገረመ ነው።

፫ኛ/ በእርግጥም ኢ-ቀኖናዊነት በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚያደርሰውን ጥፋትና በደል እንኳን ከልጅነት እስከ ዕውቀት በአገልግሎት የቆየሁት ብቻ ሳልሆን ምእመናንና ምእመናት የሚገነዘቡት ስለሆነ፣ እኔን በዚህ የጥፋት ቀለበት ውስጥ ማስገባቱ ለማን ምን እንደሚጠቅም አምላክ ይመርምረው ከማለት በስተቀር ሌላ የምለው አይኖረኝም።

ከዚህ ቀጥሎ በትኅትና የማሳስበው፣ ከዐፀደ ቤተ ክርስቲያን ደርቆ የወደቀ እንጨት ለማገዶ እንስቶ ወደ ቤቷ እዳይመጣ እናቱ አስጠንቅቃ ያሳደገችው መርዓዊ መንግሥታዊ አካል "የሃያ ሰዎች አስከሬን አንስተናል ፣ ለአፈር ምርመራ ወደ ገዳሙ ገብተናል፥ ግድቡ ተገንብቶ ከአለቀ ባኋላ ለጊዜው አራት አብያተ ክርስቲያናት ይነሳሉ ወደፊትም ሌሎች ይኖራሉ" ብሎ ያመነውንና የተናገረውን በማስመልከት በሰላማዊ መንገድ የአቤቱታ ድምፅን ማሰማት ከቀኖና ጋር ግንኙነት ካለው ከቅዱስነትዎ ፊት ቀርቤ ቅጣቴን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ።

፬ኛ/ጠቅላይ ቤተ ክህነትና የውጭ ግንኙነት መምሪያ በጽሑፍም ሆነ በቃል ስለ ዋልድባ ጉዳይ ቅድመ ማብራሪያ እንዲሰጠን ከእኛ በኩል አንዳችም የቀረበ ነገር እንደሌለ ተደርጎ ለቀረበው፤ መጋቢት 24 ቀን 2004 ዓ.ም. ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራአስኪያጅ ለብፁዕ አቡነ ፊልጶስና መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ.ም. በጀርመን ለኢትዮጵያ አምባሳደር ለክቡር አቶ ፍሥሐ አስገዶም የተጻፉትን ደብዳቤዎች አባሪ አድርጌ ከማቅረብ በቀር ሌላ የምለው የለኝም። ይህንን ደብዳቤ በፖስታ ቤት ብቻ ሳይሆን በፋክስም ጭምር ልኬ ነበር። እንደዚሁም በተመሳሳይ መልኩ በጀርመን ለኢትዮጵያ ጀኔራል ቆንሱላ በዋልድባ ዙሪያ ስጋታችንን የገለጽን መሆናችን ይታወቅልን። ከዚህም ሌላ ጠቅላይ ቤተ ክህነትና የመንበረ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤቶች "ወደ ዚያ ሂዱ፤ ወደ ዚህ ኑ፤ ዕገሌን ተቀበሉ፣ ለዚህ ክፈሉ" ከማለት አልፈው ለተጻፈላቸው ደብዳቤ መልስ የሰጡባቸው ጊዜያት ቢኖሩ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ።

፭ኛ/ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ተወክለው የሄዱ ከሰሜን ጎንደር አካባቢ ከተለያዩ ኅብረተ ሰቦች የተቀናጁ፣ በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ካህናት በቦታው ተገኝተው የሰጡት ምስክርነት እርግጠኛ ከሆነ ይህ አስደሳችና መልካም ዜና ነው። አቤቱታውን ካቀረቡት፣ ለእሥራት ከተዳረጉት፣ ከመኖሪያ ገዳማቸው ከተፈናቀሉት አባቶች አንደበት ብንሰማው እንዴት ደስ ባለን፤ ስጋታችንም ሆነ ኃዘናችን ምንኛ በተቀረፈ።!

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን፣

እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነቴ ደብዳቤ ከቅዱስ አባታችን እስከ ደረሰኝ ድረስ በመጨረሻ የማቀርበው ጥያቄ አንድ ብቻ ነው። ቅዱሱ የዋልድባ ገዳም አይነካም የሚለውን እንቀበልና የአካባቢው ወንዝ ዛሬማ ተገድቦ ለስኳር ልማት እስከዋለ ድረስ የርሻ ቦታ አስፈላጊ ነው። በዚህ ጊዜ ከገዳሙ ጋር ዘመን ያስቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት አይፈርሱም የአጥቢያው ነፍስ ወከፍ አይፈናቀልም የሚል መልስ ከተሰጠን የዕድለኞች ዕድለኞች ነን። የልማቱም ደጋፊዎች እንጂ ተቃዋሚዎች አይደለንም። እስካሁንም ከነፍስ አድን ጥሪ ጀምሮ ከእናት ቤተ ክርስቲያናችን ጎን ያልተለየንና ከቅዱስ አባታችን መመሪያ ያልወጣን መሆናችንን እያስገነዘብኩ እኔም ግዳጄን በማጠናቀቅ ላይ እገኛለሁ።

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን፣

በነገረ መለኮት ቀኖናዊ ትምህርት በቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያትና በማርገፅ ቅዱስ ጊዮርጊስ፤ በሙሉ ቤት ቅዱስ ሚካኤል፤ በድል ሰቆቃ አቡነ አረጋዊ፤ በእጣኖ ቅድስት ማርያም አብያተ ክርስቲያናት (ወዘተ) መካከል ምንም ዓይነት የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል ልዩነት እንደሌለ ቅዱስነትዎ ያውቀዋል። ለዚህ መረጃ ከተሰጠኝ "ለስሂት መኑ ይሌብዋ" ስህተትን ማን ያስተውላታል እንደተባለው ነውና ቅዱስነትዎንና ቤተ ክርስቲያኔን እንደበደልሁ ቆጥሬ ሰባት ጊዜ ሰባ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

የቅዱስ አባታችን ሐዋርያዊ ቡራኬዎ ይድረሰኝ

ልጅዎ

ሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀ
በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
- ለጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ጽ/ቤት
- ለኢፌድሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለክቡር አምባሳደር አቶ ፍሥሐ አስገዶም
- ለክቡር አቶ ሙሉጌታ ዘውዴ
  ቆንስል ጀኔራል
- ለአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት
  <u>ጀርመን</u>